# ለከርሞም ኑሮ አለና ከወዲሁ ይታሰብበት !

**ኢብሳ ነመራ** 02-20-17

ኢትዮጵያ ለድርቅ ተጋላጭ ከሆኑ የዓለማችን አገራት አንዷ ነች። ቢዘገይ በየአስር ዓመቱ አንዴ በድርቅ ትመታለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የድርቁ ድግግሞሽ ወደአምስትና ከዚያ በታች ዓመት እያጠረ ነው። የአለፉትን አስር ዓመታት እንኳን ብንመለከት በ1994፣ በ2003፣ በ2007፣ ዘንድሮ በ2009 ዓ/ም የድርቅ አደጋ ተከስቷል። በእነዚህ መካከልም  ተጽዕኗቸው በጥቂት አካባቢ የተወሰነ በመሆኑ ጎልተው ያልወጡ ጥቃቅን የድርቅ ክስተቶች አጋጥመዋል። ታዲያ ኢትዮጵያ በእነዚህ ዓመታት ለድርቅ አደጋ ምክንያት የሚሆኑ የተፈጥሮ አካባቢ ልማትና እንክብካቤ ስራዎች ሰርታለች። ይህ የተፈጥሮ አካባቢ ልማትና እንክብካቤ የግብርና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ አስተዋጽኦ እንዳለው ቢታመንም፣ አደገኛ ድርቅን ማስቀረት ግን አልቻለም። ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያን የሚመታት ድርቅ ከቁጥጥሯ ውጭ የሆነ ተፈጥሯዊና በተለይ የበለጸጉ አገራት በዓለም የአየር ንብረት ላይ በሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽእኖ የተፈጠረ መሆኑን ያመለክታል።

ይሁን እንጂ፤ ባለፉት ሃያ ዓመታት በአማካይ በየአምስት ዓመቱ የተከሰቱትንና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለምግብ እጥረት ተጽእኖ ያጋለጡ የድርቅ አደጋዎች እንደ 1976/77፣ 1965/66 እና ከዚያ ቀደም በየአስር ዓመቱ ሲከሰቱ እንደነበሩ ድርቆች ወደረሀብነት ተለውጠው ለዜጎች ህይወት መጥፋትና ለስደት ምክንያት አልሆኑም። የዚህ ምክንያት መንግስት ድርቁ እንደተከሰተ የከፋ ተጽእኖ ማሳደር ሳይጀምር ችግሩን ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በማሳወቅ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ማቅረብ በመቻሉ ነው። በተለይ በ1985/86 እና በ1994 ዓ/ም የተከሰተውን የድርቅ ተጽእኖ በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ሳያደርስ መከላከል የተቻለው በዚህ ሁኔታ ነው። ከዚህ በኋላ በ2003፣ በ2007/8 እና ዘንድሮ የተከሰተውን ድርቅ ደግሞ የውጭ እርዳታ ሳይደርስ በራስ አቅም መከላከል የተቻለበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

ይህ አቅም በአገሪቱ በተመዘገበው ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት የተፈጠረ ነው። በአገሪቱ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት በተመዘገበው ፈጣንና ተከታታይ እድገት ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የሚውል በቂ የመጠባበቂያ የእህል ክምችት የመያዝ አቅም ተፈጥሯል። በ2007 በበልግና በክረምት ዝናብ እጥረት ድርቅ ሲከሰት አገሪቱ 450 ሺህ ሜትሪክ ቶን የመጠባበቂያ የእህል ክምችት ነበራት። ዘንድሮም ተመሳሳይ የመጠባበቂያ የእህል ክምችት አለ። በቀጣይ ይህን የእህል ክምችት ወደ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ለማሳደግ ታቅዷል። በተለይ በዘንድሮው መኸር የተመዘገበው የ12 በመቶ የግብርና ምርት እድገት ኢትዮጵያ ከአገር ውስጥ ገበያ ይህን የመጠባበቂያ የእህል ክምችት ማሰባሰብ እንደምትችል ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት የድርቁን ተጽእኖ ለመቋቋም የሚያስችል በጀት የመመደብ አቅም አለው። በ2008 ዓ/ም መንግስት የድርቁን ተጽእኖ ለመከላከል የ16 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ በጀት መድቦ እንደነበረ ይታወቃል። ይህ ማለት ግን የድርቅን ተጽእኖ ለመቋቋም ምንም የውጭ እርዳታ የማያስፈልግበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ማለት አይደለም። ከዚህ ይልቅ መንግስት የድርቅ ተጽእኖ እንደደረሰ የውጭ እርዳታ ለመጠበቅ በሚወስደው ጊዜ ጉዳት ሳይደርስ በራስ አቅም ፈጥኖ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ በመስጠት ጉዳት ሳይደርስ ተጽእኖውን መከላከል የተቻለበት ደረጃ ላይ መደረሱን የሚያመለክት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የውጭ እርዳታ ቢያስፍልግም፣ በእርዳታ አሰጣጡ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው መንግስት የሆነበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። እዚህ ላይ ባለፈው ዓመትና ዘንድሮ በተከሰተው ድርቅ የቀረበው አብዛኛው የምግብ እርዳታ ከረጢት የኢፌዴሪ መንግስት አርማ የነበረበት መሆኑን ልብ ይሏል።

እንግዲህ ባለፈው ዓመት የተከሰተውን በአስከፊነቱ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ከተከሰቱተ ሁሉ ቀዳሚ የነበረውን 10 ነጥበ 2 ሚሊዮን ዜጎችን ለምግብ እጥረት ያጋለጠ ረሃብ የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ፣ አንድም ሰው በምግብ እጥረት ምክንያት ከመኖሪያ ቄዬው ሳይፈናቀል፣ ህጻናትና ወጣቶች ትምህርታቸው ሳይስተጓጎል መከላከል ተችሏል። በዚህ የ2007 ድርቅ የምግብ እጥረት የተከሰተባቸው አብዛኞቹ አካባቢዎች ከዘንድሮው የድርቅ ተጽእኖ ነጻ ናቸው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአምናው ተጽእኖ የቀጠለባቸው ጥቂት ኪስ አካባቢዎች ብቻ ናቸው።

ይሁን እንጂ፤ ዘንድሮም አገሪቱ በድርቅ ተመትታለች። የዘንድሮው ድርቅ የተከሰተው በኦሮሚያ ቦረናና ጉጂ ዞኖች፤ በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ በአፋርና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ነው። እነዚህ አካባቢዎች ቆላማና ዝናብ አጠር የአየር ንብረት ያላቸው በመሆኑ ለድርቅ ተጋላጮች ናቸው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩትም አርብቶ አደሮች ናቸው። በአጠቃላይ የዘንድሮው የድርቅ ተጽእኖ በቆላማና የአርብቶ አደር መኖሪያ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተ ነው። በዚህ ድርቅ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች ለምግብ እጥረት ተጋልጠዋል። እናም የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

በዚህ ድርቅ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ማቅረብ ያስፈለገው ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትም ጭምር ነው። የአርብቶ አደሩ ኑሮ በእንስሳት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የአርብቶ አደሩን ቀጣይ ህይወት አስተማማኝ ለማድረግ የከብት መኖና ውሃ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኗል። ይህ ሁኔታ የእርዳታ አሰጣጡን አስቸጋሪ ያደርገዋል።

በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ላይ የሚደርስ የድርቅ ተጽእኖ ከአርሶ አደሩ በተለየ ጉዳቱ ፈጣን፣ የእርዳታ አሰጣጡም ውስብስብና አስቸጋሪ ነው። የድርቁን ጉዳት ተጽእኖ ፈጣን የሚያደርገው፣ አርብቶ አደሩ ለከርሞ ብሎ የሚያስቀምጠው ምንም የእህል ክምችት የሌለው መሆኑ ነው። የአርብቶ አደሩ ኑሮ በየእለቱ ከከብቶቹ ከሚያገኘው ተዋጽኦ - ወተት፣ ቅቤ፣ ደምና በተወሰነ ደረጃ በስጋ ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህ ምግቦች ደግሞ ምን ቢትረፈረፉ በጎተራ አይከማቹም። እናም አርሶ አደሩ የምግብ ዋስትና የሚኖረው ከብቶቹ ጤናማ ሆነው እስከኖሩ ድረስ ብቻ ነው። ድርቅ ተከስቶ የከብቶች ሳርና ውሃ ሲጠፋ አርብቶ አደሩ ምንም ፋታ ሳይኖረው ለምግብ እጥረት ይጋለጣል።

ከዚህ በተጨማሪ፤ አርብቶ አደሩ ድርቁ ካለፈ በኋላ በቀላሉ አያገግምም። ምክንያቱም በድርቁ አስከፊነት ልክ ከብቶቹ ስለሚያልቁ፤ አርብቶ አደሩ እንደምንም የራሱን ህይወት የድርቁን ዘመን አሻግሮ ማትረፍ ቢችል እንኳን፤ የአየር ሁኔታው ከተስተካከለም በኋላ ለምግብ እጥረት የሚጋለጥበት ሁኔታ አለ። ይህ እንዳይሆን የእርዳታ አሰጣጡ ለከብቶች መኖና ውሃ ማቅረብንም ያጠቃልላል። ይህ ካልተቻለ ከብቶቹን ሸጦ ከድርቁ በኋላ  መልሶ መግዛት የሚያስችለው ገንዘብ በእጁ መያዝ አለበት። ቢያንስ ለዘር የሚሆኑ ከብቶች - ጊደሮችና ጥጆች መኖ እንዲያገኙ ካልተደረገ የአርብቶ አደሩ ህይወት ከድርቁም በኋላ ፈታኝ መሆኑ አይቀሬ ነው። በሌ በኩል፤ አርብቶ አደሩ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስ በመሆኑና ከዚህ የአኗኗር ዘይቤው በመነጨ የመሰረተ ልማት ማስፋፋት አስቸጋሪ ስለሚሆን በአብዛኛው የተሟላ መሰረተ ልማት የሌለበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይህም ፈጣን እርዳታ የማቅረቡን ስራ ፈታኝ ያደርገዋል።

እንግዲህ ዘንድሮ ለድርቅ ተጽእኖ የተጋለጠው የዚህ አይነት ውስብስብ ሁኔታዎች ያሉት የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ነው። ይሁን እንጂ፤ የኢፌዴሪ መንግስትና ድርቁ የተከሰተባቸው ክልላዊ መንግስታት ይህን የአርብቶ አደር የተለየ ባህሪይ ባገናዘበ መልኩ የአስቸካይ ጊዜ ምግብና የእንስሳት መኖ እንዲሁም ውሃ እያቀረቡ ነው።

የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ባለፈው ወር በፈረንጆቹ 2017 ለሰብዓዊ እርዳታ በሚያስፈልገው ገንዘብ ዙሪያ ከአለም አቀፍ ለጋሽ ተቋማት እና አገራት ጋር  ተወያይቷል። ኮሚሽኑ ኢትዮጵያ የተከሰተውን ድርቅ

የተቋቋመችበትን መንገድ፣ የተገኘውን ውጤትና በፊረንጆቹ 2017 የዕለት ደራሽ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች ቁጥር የተለዩባቸው የዳሰሳ ጥናቶች አካሂዶ ይፋ አድርጓል። በድርቁ ሳቢያ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች የዕለት ደራሽ እርዳታን ጨምሮ ሰብዓዊ ድጋፍ ለማቅረብ 948 ሚሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግም ኮሚሽኑ ገልጿል። ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ካለፈው የተሸጋገረ በጀት ታሳቢ ሲደረግ 715 ሚሊዮን ዶላር በተጨባጭ እንደሚያስፈልግም አመልክቷል።

እስካሁን ወዳለው የእርዳታ አሰጣጥ ስንመለስ፣ የፌዴራል መንግስት የ1 ቢሊዮን ብር በጀት መድቦ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ በማቅረብ ላይ ይገኛል። ከዚህ ጎን ለጎን ድርቁ የተከሰተባቸው ክልላዊ መንግስታትም በጀት መድበው የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች 60 ሚሊዮን ብር መድቦ ድጋፍ እያደረገ ነው። የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግስትም 300 ሚሊዮን ብር መድቦ ለድርቁ ተጽእኖ ምላሽ እየሰጠ ይገኛል። የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ደግሞ ከፓርኮች መኖ ሰብስቦ በማምጣት ከፌዴራል መንግስት ከተሰጠው መኖ ጋር ቀላቅሎ ለእንስሳቱ እያቀረበ ይገኛል። በአጠቃላይ፤ የዘንድሮው የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አሰጣጥ ሲገመገም በአንድም ሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንደማይደርስ፤ አንድም ሰው በምግብ እጥረት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢው እንደማይሰደድ፤ ተማሪዎችም ትምህርታቸው እንደማይስተጓጎል እርግጥኛ ነው።

ይሁን እንጂ፤ የእንስሳት መኖ በማቅረብ ረገድ ችግሮች ታይተዋል። ከብቶች ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው በተጨማሪ የክብር መግለጫ በሆኑበት የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ ከሰው ቁጥር እስከመቶ እጥፍ የሚበልጥ የከብት ቁጥር እንደሚገኝ ይገመታል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በቂ በጀት ቢኖር እንኳን ለዚህ ሁሉ መኖ (ሳር) ማቅረብ አስቸጋሪ ነው። በዚህ ምክንያት በርካታ ከብቶች አልቀዋል። በመሆኑም ለሁሉም እንስሳ መኖ ማቅረብ ስለማይቻል አርብቶ አደሩ በቀጣይ ለዘር የሚሆኑትን ጊደሮችና ኮርማዎች ብቻ አስቀርቶ የተቀረውን ለገበያ እንዲያቀርብ ጥረት እየተደረገ ነው። ሆኖም፤ በአርብቶ አደሩ አቅራቢያ ባሉ ገበያዎች ከብቶች በገፍ ስለቀረቡ ዋጋቸው እጅግ ወድቋል። ከዚህ በተጨማሪ፤ በአነስተኛ ዋጋም ቢሆን አቅርቦቱ ገበያው ከሚሸከመው በላይ በመሆኑ መሸጥ የማይቻልበት ሁኔታም ተፈጥሯል። ከብቶቹ በመኖ እጥረት የተጎዱ መሆናቸው ደግሞ ሁኔታውን አባብሶታል። ይህም ሆኖ ግን፤ ከብቶቹ ታርደው ስጋውን በቋንጣ መልክ በማዘጋጀት በተለይ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ ለመከላከያ ሰራዊት፤ ወዘተ. ለገበያ ለማቅረብ እየተሞከረ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን የመኖ ማቅረቡም ተግባር እየተከናወነ ይገኛል።

በዚህ ረገድ በኦሮሚያ፣ በደቡብ እና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች ከ200 ሺህ በላይ እስር መኖ መሰራጨቱን የብሄራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታውቋል። አንድ እስር መኖ አራት ያህል ከብቶችን የመመገብ አቅም አለው። ክልሎችም የእንስሳት መኖ በማቅረብ በኩል የራሳቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የደቡብ ክልል 100 ሺህ እስር መኖ፤ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል 70 ሺህ እስር መኖ በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች አሰራጭተዋል። ከዚህ በተጨማሪም ለስኳር ምርትነት የማይውል የሸንኮራ አገዳ ምርት እየተለየ ችግሩ ባለባቸው አካባቢዎች እየተሰራጨ ይገኛል። ከችግሩ አሳሳቢነት አኳያ በፓርኮች ውስጥ ያለው ሳር እየታጨደ ድርቁ በተከሰተባቸው ሶስት ክልሎች እየተዳረሰ መሆኑም ታውቋል። በአንድ ወርና በአስራ አምስት ቀናት የሚደርሱ የመኖ ምርቶችን በማምረት ችግሩን በቀጣይ ለመከላከልም እየተሰራ ነው።

በአጠቃላይ፤ ዘንድሮ የተከሰተው ድርቅ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን በማጥቃቱ የእርዳታ አሰጣጡ ውስብስብና አስቸጋሪ ቢሆንም በአንድም ሰው ህይወት ላይ ጉዳት በማይደርስበት፤ አንድም ሰው ከመኖሪያ ቀዬው በማይፈናቀለበትና ትምህርት በማይስተጓጎልበት ሁኔታ የተጠናከረ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የማቅረብ ስራ እየተከናወነ ነው። በአርብቶ አደሩ እጅ ያሉትን

ሁሉንም ከብቶች ማትረፍ የሚያስችል መኖ ማቅረብ አዳጋች ቢሆንም፤ አርብቶ አደሩ ከድርቁ በኋላ ራሱን ችሎ መኖር የሚያስችለው የከብት ዝርያና በተወሰነ ደረጃም ያጣቸውን ከብቶች ገዝቶ መተካት የሚያስችለው ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው። ሆኖም ዘለቄታዊ መፍትሄ ስላልሆነ አርብቶ አደሩ ለድርቅ የማይበገር የኑሮ ዘይቤ እንዲከተል የማድረግና በተለይ የውሃ ልማትን ማዕከል ያደረጉ ስራዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊሰሩ ይገባል። ከዘንድሮም ባሻገር ህይወት/ኑሮ አለና የአርብቶ አደሩን ዘላቂ ልማትና ድርቅን የመቋቋም አቅም የመገንባት ጉዳይ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል።